# ለቀለም ቅብ ሥራ ተቋራጮች መረጃ

የታደሰበት ዕለት ሰኔ 2017

## የ PaintCare የቀለም ቅብ ኃላፊነትን የመወጣት ፕሮግራሞች የሥራ ተቋራጮች የተራረፉ ቀለሞችን ዳግም አድሰው ጥቅም ላይ እንዲያውሉ እና በአግባቡ እንዲያስወግዱ ምቹ መንገዶችን ያቀርባሉ።

የቀለም አምራች ድርጅቶች ከፍጆታ የተረፈውን ቀለም በሁሉም ክፍለ ግዛቶችና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት [ዋሽንግተን አካባቢ] በአግባቡ በተዘጋጀው የቆሻሻ ቀለም ማጠራቀሚያ ቦታ [PaintCare states] ተሰብስቦ እንደገና በሂደት ታድሶ [ሪሳይክል] ለጥቅም እንዲውል ያደርጋል። በዚህ መሰረት የቤተሰብ አባወራውችና ሌሎች ድርጅቶች ከፍጆታ የቀረውን ቀለም ከተጠራቀመበት ቦታ በነጻ ያለምንም ክፍያ እንዲወስዱ የሚያስችል ለዚህ ተብሎ የተደነገገ የቀለም ዋስትና ሕግ ይፈቅዳል።

ለነዚህ ፕሮግራሞች የስራ ማስኬጃ የሚውለው ገንዘብ የሚሰበሰበው ከአርኪቴክት ስራዎች (የቤት ቅብ፣ ያደፉ ግድግዳዎች እደሳ፣ ቫርኒሽ ... ወዘተ) በሚገኘው ሽያጭ ነው።

### የቀለም ቅብ ሥራ ኃላፊነትን መወጣት

የእነዚህ የቀለም ቅብ ሥራ ኃላፊነትን የመወጣት ፕሮግራሞች ዋንኛ ግቦች የሚባክን ቀለምን መቀነስ እና የተራረፈ ቀለምን ለአካባቢ ጥበቃ በሚስማማ መልኩ እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሥርዓት በመጠቀም ማስተዳደር መቻል ነው። ፕሮግራሞቹ በ PaintCare የተባለው ለትርፍ ያልቆመ የአሜሪካ የቀለም ቅቦች ማህበር (American Coatings Association (ACA)) የተቋቋመ ድርጅት አማካይነት የተዘጋጁ እና የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

ፔይንትኬር [PaintCare] በ ካሊፎርኒያ፣ ኮሎራዶ፣ ኬነዲኬት፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ ሜይን፣ ሚነሶታ፣ ኦሪገን፣ ሮድ አይላንድ፣ እና ቬርሞንት ፕሮግራሞች አሉት።




### ክፍያዎች እና የገንዘብ ድጋፍ

በየክፍለ ግዛቱ ያለው ሕግ እንደሚያዘው የቀለም አምራች ድርጅቶች ለአርክቴክት ስራዎች ጅምላ ሽያጭ የሚውለውን የፔይንትኬር ክፍያ ዋጋ [PaintCare Fee] ለነብስ ወከፍ ክፍለ ግዛት መተመን አለባቸው። ክፍያው ከ $0.35 እስከ $1.99 ይደርሳል። ክፍያው በቀለም መያዣው መጠንና [container size] እንደየ ክፍለግዛቱ [state] የለያያል። ዝርዝሩን እታች ተመልከት።

$0.35 - $0.49: ትናንሽ መያዣዎች (አብነት፥ ፓይንትና ኳርት)

$0.75 - $0.99: መካከላኛ ማጠራቀሚያዎች (አብነት፥ አንድ ጋሎን)

$1.60 - $1.99: ትላልቅ ማጠራቀሚያዎች (አብነት፥ እስከ አምስት ጋሎን)

በሚኖሩበት ክፍለግዛት ያለው የፔይንትኬር [PaintCare] ያከፋፈል መርጃ ለማግኘት እባኩዎን ይህ ድረ-ገጽ [paintcare.org/fees] ይመልከቱ።

ክፍያው በቀለም አምራች ድርጅቶች ለፔይንትኬር PaintCare ፕሮግራም ይከፈላል። ገቢው ደግሞ ለስራ ማስኬጃ፣ ቀለሙ የምጠራቀምበትና የሚነሳበትን ቦታዎች ለምዘጋጀት፣ ለሪሳይክል ሂደት፣ እንዲሁም ባግባቡ የሚወገድበት መንገድ ለመቀየስ ይውላል። በተጨማሪ ክፍያዎቹ ለሸማቾች ትምህርት እና ለፕሮግራም አስተዳደር ወጪ መሸፈኛ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ሕጉ በተጨማሪ ሁሉም አከፋፋዮች እና ቸርቻሪ ነጋዴዎች የ PaintCare ክፍያን ከእነርሱ የመሸጫ ዋጋ ላይ በግዛቱ ውስጥ በሚሸጡት ቀለም ዋጋ ላይ እንዲያካትቱ ይጠይቃል።

## ለስራ ተቋራጭ ኮንትራክተሮች የሚሆን ምክር

### የእናንተን የዋጋ ግምቶች ማዘጋጀት

የሥራ ዋጋዎችን በመገመት ወቅት፣ የሥራ ተቋራጮች የሚሰጡት የሥራ ዋጋ እነዚህን ክፍያዎች ያካተቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለቀለም ነክ ምርቶች ከአቅራቢዎች ጋር በመነጋገር እነዚህን ክፍያዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

### ክፍያዎችን ወደ የእናንተ ደንበኞች አስተላልፉ

PaintCare ሥራ ተቋራጮች የሚከፍሏቸውን ክፍያዎች መልሰው ለመቁረጥ እንዲችሉ ከእነርሱ ደንበኞች ክፍያዎችን በደንበኞቻቸው ላይ እንዲያስቡዋቸው ይመክራል። በተጨማሪ በእናንተ የዋጋ መጠየቂያዎች ላይ እነዚህን ክፍያዎች እንዳካተታችሁ የእናንተ ደንበኞች እንዲያውቁ ማድረግ አለባችሁ።

### ግንባታ ሥራቸው ከተጠናቀቁ ቦታዎች ቀለሞችን ማጽዳት

ፔይንትኬር [PaintCare] ከፍጆታ የቀረ ቀለም የሚከማችበት ከ 90 እስከ 95 በመቶ የፔይንትኬር አገልግሎት በሚሰጥባቸው ክፍለግዛቶች

ወይም ስቴቶች በ 15 ማይል (ወደ 24.14 ኪሎ ሜትር) ርቀት ላይ የመሰብሰቢያ ቦታዎች ያዘጋጃል።

አብዛኛዎቹ ቀለም የሚጣልባቸው ቦታዎች የቀለም ማከማቻ መጋዘኖች ናቸው። ሌሎች የቆሻሻ ማሸጋገሪያ ጣቢያዎች፣ የመልሶ በማደስ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከሎች፣ እና በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው የቤት ውስጥ አደገኛ ቆሻሻ የማስወገድ ፕሮግራሞችን ያካታትሉ። በቀለም መጣያ ቦታ መሳተፍ በበጎ ፈቃድ የሚደረግ ነው። ቀለም መጣያ ለማግኘት፣ የእኛን የድር ጣቢያ ይጎብኙ።

በእነርሱ ግዛት ውስጥ የቀለም መጣያ ቦታዎች በሚመቹ ቦታዎች ላይ ሲዘጋጁላቸው ሁሉም ሰዎች የተረፉ ጥቂት የቀለም ጋሎኖችን የማይፈልግ ቀለምን በዓመት እንዲጥሉ ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል። አብዛኛዎቹ በ PaintCare ግዛቶች ውስጥ ያሉ የሥራ ተቋራጮች የማከማቻ ቦታቸውን ያጸዱ ሲሆን ቀለም ማጠራቀምንም ትተዋል። ሌሎች ደግሞ የእነርሱ ደንበኞች ከእንግዲህ የማይፈልጉትን ቀለም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጥያቄ በሚያቀርቡላቸ ጊዜ መልስ ለመስጠት በመቻላቸው ደስተኞች እንደሆኑ እና ደንበኞቻቸው የቀለም መጣያዎቹን መጠቀም እንዳለባቸው ምክር እንደሚሰጡ ይናገራሉ።

### በንግድ ተቋማት የቀለም መጣያ ቦታዎች አጠቃቀም

በየወሩ 220 ዋውንዲ (99.79 ኪ.ግራም) በታች የሚሆኑንት አደገኛ የሆኑ ተረፈ ምርትን* የሚያመርቱ መሥሪያዎች ሁለቱም የውሃ ቀለም - እና የዘይት ቀለም (የዘይት ቀለም መጠን ላይ መጠነኛ እገዳዎች ተደርገውበት) ሊጥሉ ይችላሉ። ማሸጋገሪያ ጣቢያዎችን እና የመኖሪያ ቤት አደገኛ ቆሻሻ ፕሮግራሞችን ከመጎብኘታችሁ በፊት ሁሉም ይህ ነገር የንግድ ተቋማትን ሊያስተናግድ ስለማይችል እና ተጨማሪ ገደቦች ሊኖሩት ስለሚችል በመጀመሪያ መቻሉን አረጋግጡ።

በየወሩ 220 ዋውንዲ (99.79 ኪ.ግራም) በታች የሚሆኑንት አደገኛ የሆኑ ተረፈ ምርትን የሚያመርቱ መሥሪይ ቤቶች ውሃ ነክ የሆኑ ምርቶችን ብቻ የፐይንት ኬር/PaintCare የሽያጭ መጣያ ቦታዎችን ይጠቀማል፤ ለዝይት ቀለም ምርቶች ቦታዎቹን መጠቀይም አይፈቀድላቸውም።

**220 ፓውንድ (99.79 ኪሎ ግራም) ከ 20 -30 ጋሎን (75.71 - 113.56 ሊትር) ቀለም ነው። መስሪያ ቤቶች ምን ያህል አደገኛ የሆኑ ተረፈ ምርቶችን እንዳመረቱ በሚቆጥሩበት ጊዜ፣ የዘይት ቀለም ይቆጠራሉ (ምክንያቱም በሕግ አደገኛ ተረፈምርት ተብሎ ተመድቧል)፤ ነገር ግን ከተለያዩ ተክሎች የሚሰሩ ቀለሞች (እና ሌሎች የውሃ ቀለሞች) በአጠቃላይ በወራዊው በ220 ፓውንዱ (99.79 ኪ.ግራም) ላይ አይቆጠሩም።*



### ለትላልቅ መጠኖች ማንሳት አገልግሎት

በጥቂቱ እስከ 200 ጋሎን (757.08 ሊትር) የሚተመን ከፍጆታ የተረፈ ቀለም ሪሳይክል እንዲደረግላቸው የሚፈልጉ ድርጅቶች ቀለሞቻቸው ከዚህ በታች በተገለጹት ዘዴዎች ሊሰበሰቡ ይቻላል
ከክፍያ ነጻ የሆነ የፔይንትኬር ኣገልግሎት ስለዚህ አገልግሎት ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለማስያዝ፣ የእኛን የድር ጣቢያ ይጎብኙ ወይም በስልክ ወይም በኢሜይል እኛን ያነጋግሩን።

## ምን ዓይነት ምርቶች የአገልግሎት ሽፋን ያገኛሉ?

በ PaintCare መጣያ ቦታዎች ተቀባይነት ያላቸው ተረፈ ምርቶች በሚሸጡበት ጊዜ ክፍያ የተከፈለባቸው ተመሳሳይነት ያላቸው ምርቶች ናቸው። የፔይንትኬር ምርቶች የሚባሉት ውጫዊና ውስጣዊ የአርክቴክት ቅብ ያላቸው ሆነው ይዘታቸው አምስትና ከአምስት ጋሎን (18.93 ኪ. ግራም) በታች ነው። ሆኖም ግን ጋዝ ነክ (aerosol) ምርቶችን (የስፕሬይ ቆርቆሮዎች)፣ የኢንዱስትሪያ ጥገና, (industrial maintenance (IM)) የኦርጂናል መሣሪያ አምራች (original equipment manufacturer (OEM)) ወይም ልዩ ሙያን የሚጠይቁ ቀለሞችን አያካትቱም።

### PAINTCARE PRODUCTS

- የውስጥ ወይም የውጭ የስነ ሕንፃ ውበት መጠበቂያ ቀለሞች፡- ላቴክስ፣ አክሪሊክ፣ በውሃ የሚበጠበጡ፣ አልኪድ፣ በዘይት የሚበጠበጡ፣ ኤናሜል (ድብልቅ ቀለሞችን ጨምሮ)
- የእንጨት ሳንቃ ያላቸው የወለል ቅቦች
- ፕሪመርስ፣ የጣራ ቀለሞች፣ ገበር ቀለሞች
- የዝገት መከላከያ ቀለሞች
- ሼላክ (shellacs) ፣ ላኬር (lacquers) ፣ ቫርኒሽና (varnishes) ዩረቴን (urethanes) የተባሉ ንጥረነገር ያለባቸው ቀለሞች
- ፀረ ውሃ ጣራ መከላከያ ኮንክሪት/የግንብ ሥራ/የእንጨት ቀለሞች እና ትንኝና ተባይ ማራቂያዎች (ሬንጅ ወይም በቢትሜን የሚበጠበጥ ያልሆነ)
- የብረት ቀለም፣ የዝገት መከላከያዎች
- የሣር እና የመስክ ቀለሞች

### የፔይንትኬር ያልሆኑ ምርቶች [NON-PAINTCARE]

- የቀለም ማቅጠኛዎች፣ ሚኒራል ስፕሪትስ፣ ማዋሃጃዎች
- ኤሮሶል ቀለሞች (ስፕሬይ ቆርቆሮዎች)
- የመኪና እና የጀልባ ነክ ቀለሞች
- የሥነጥበብ ቀለሞች
- ኮልኪንግ አጥሮች፣ ኤፖግዚስ፣ ማጣበቂያዎች፣ ኮላዎች፣ ማስቲሾች
- የቀለም ተጨማሪዎች፣ ቀለም መልክ መቀየሪያዎች፣ ቀለም መቀየሪዎች፣ ሬሲንስ
- የእንጨት ዕድሜ መጠበቂያ ኬሚካሎች (ጸረ ተባይ መርዝ የያዙ)
- የጣራ ማጣበቂያ እና ጥገና
- የአስፋልት፣ ሬንጅ እና በቢትማን የሚበጠበጡ ተረፈ ምርቶች
- ባለ2-ክፍለ አካል ቀለም መቀቢያዎች
- የዴክ አጽጂዎች
- ትራፊክ እና የመንገድ ምልክት ቀለሞች
- የኢንዱስትሪያዊ ጥገና (Industrial Maintenance (IM)) ቀለም ቅቦች
- ኦርጂናል የመሣሪያ አምራች (Original Equipment Manufacturer (OEM)) (የሱቅ መተግበሪያ) ቀለሞች እና ማሳመሪያዎች